**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ**
**እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ**
**ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ-ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ**
**ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ**

**The Triumphant Lion of the Tribe of Judah**
**God The Son Jesus Christ**
**Eternal Priest in the Order of Melke-Zedeq the Ethiopian**
**King of Zion and King of Kings of Ethiopia**

**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር**
**እግዚአብሔር እም፡ድንግል ማርያም**
**እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ**
**ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ**

**Ethiopia Stretches out Her Hands to God**
**God The Mother Virgin Mary**
**Mother of Our Messiah and Our Holy Mother**
**Queen of Zion and Queen of Queens of Ethiopia**

# ኪ ዳ ና ች ን

# K I D A N A CH ' N


**ልዩ ዕትም፡ መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻፱ (፪ሺ፱) ዓመተ ምሕረት።**

Special Edition: Meskerem 1, 2009 A.D (September 11, 2016)


**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥**
**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና**
**የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡**
**በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"**
**to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

# ልዑል እግዚአብሔር፡

ከዘመነ ዮሓንስ፡ ወደዘመነ ማቴዎስ አሸጋግሮ፡

## የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን፡

የ፯ሺ፭፻፱ (የሰባት ሽህ አምስት መቶ ዘጠኝ)ኛውን

ዓመተ-ልደቷንና የነጻነት ህልውናችንን በዓል፣

እንዲሁም፡

## የአዳምና የሔዋንን ልደት፥

## የቅዱሱ ኪዳን፡ መነሻ የኾነው ሥርዓተ ጋብቻም

## የተከሠተበትን ቀን ያካተተውን፡ የፍጥረትን መገኛ

፯ሺ፭፻፱ኛውን ዓመት በዓል፥

ደግሞም፡

## የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡

የ፪ሺ፳፭ (የኹለት ሽህ ሃያ አምስት)ኛውን ዓመት

እና

## የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡

የ፪ሺ፱ (የኹለት ሽህ ዘጠኝ)ኛውን ዓመት፡

## የልደታት በዓል

ለማክበር ለበቃንበት፡ ለአዲሱ፡ የ፪ሺ፱ (፳፻፱)

(ኹለት ሽህ ዘጠኝ፥ ወይም፡ ሃያ መቶ ዘጠኝ፥ ወይም፡ ዕሥራ ምእት ወተሰዓቱ)

ዓመተ-ምሕረት፥ መስከረም ፩ ቀን፣

እንኳን፡ በያለንበት፡ በሰላም አደረሰን!

\+ \+ \+

# ርእሰ አንቀጽ

እግዚአብሔርን፥ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ልጆች በሚመለከት፡ በብሉዩ ኪዳን ነቢይ፡- **"እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ-ዓለም፤ ወገብረ መድኃኒተ፡ በማእከለ ምድር፤ አንተ አጽናዕካ፡ ለባሕር በኃይልከ፤ ወአንተ ሰበርከ ርእሰ-ከይሲ፡ በውስተ ማይ፤ ወአንተ ቀጥቀጥከ፡ አርእስቲሁ ለከይሲ። ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ-ኢትዮጵያ!**

*"ዓለሙን ከመፍጠርህ በፊትም ኾነ፡ በኋላ፡ ምንጊዜም፡ ንጉሣቸው የኾንከውና በምድር መካከል፡ መድኃኒትን* **[በኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም]** *ያደረግህ፥ ባሕርንም፡ በኃይልህ* **[በኢትዮጵያው ኢየሱስ መሲሕ]** *ያጸናህ፥* **[በእርሱ፡ በሰላምህ]፡** *የእባቡን ጭንቅላት፡ በውኃ ውስጥ የሰበርህ፥ የዘንዶውንም ራሶች የቀጠቀጥህ፡ አንተ እግዚአብሔር፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብህ፥ የቅድስት እናትህ፡ የድንግል ማርያምም ልጆች ለኾኑት፡ ለኢትዮጵያ ሰዎች፡ የሚያስፈልጋቸውን ሲሳይ ኹሉ ሰጠሃቸው!"* ተብሎ የተነገረ የትንቢት ቃል መኖሩ ይታወቃል።

በዚህ ረገድ፡ በአዲሱ ኪዳን ባለራእይ የተነገረውንና የተጻፈውን ደግሞ መመልከት ነው፡- **"ወሶበ ርእየ ዝክቱ አርዌ፡ ከመ ወድቀ ውስተ ምድር፣ ዴገና ለእንታክቲ ብእሲት፡ እንተ ወለደት ሕፃነ ተባዕተ። ወተውህባ ለይእቲ ብእሲት፡ ክልኤ ክንፍ፡ ከመ ዘዐቢይ ንስር፡ ከመ ትሥርር ውስተ ገዳም፥ ወውስተ መካን፡ ኅበ ትትዐቀብ በኵሉ መዋዕል...እምቅድመ ገጹ ለውእቱ አርዌ። ወሠረረ፣ ወዴገና፡ ውእቱ አርዌ። ወአውፅአ እምነ አፉሁ፡ ውእቱ አርዌ፡ ማየ ብዙኀ፡ እንተ ድኅሬሃ፡ ለይእቲ ብእሲት፡ ከመ ፈለግ ዐቢይ፡ ከመ ይንሥአ ውኂዙ። ወረድአታ ምድር፡ ለይእቲ ብእሲት፤ ወአርኀበት አፉሃ ምድር፤ ወሰረበቶ፡ ለውእቱ ውኂዝ፡ ዘአውኀዘ፡ ውእቱ አርዌ፡ እምነ አፉሁ። ወኢያእመረ፡ ከመ ተውህበ ላቲ ክንፍ። ወተምዐ ውእቱ አርዌ፡ ላዕለ ይእቲ ብእሲት። ወሖረ ይፅብአሙ፡ ለእለ ተርፉ ውሉዳ፤ ወለእለ የዐቅቡ ትእዛዘ እግዚአብሔር፤ ወይሄልዉ በጽድቁ፡ ለኢየሱስ መሲሕ። ወቆመ ውእቱ አርዌ፡ ላዕለ ኖጻ ባሕር።**

*"ይኼ አውሬ (ዲያብሎስ)፡ ወደምድር እንደወደቀ ባየ ጊዜ፡ ወንድ ሕፃን የወለደችውን፡ ይህችን ሴት አሳደዳት። ይህችም ሴት፡ ከዚሁ አውሬ ፊት ርቃ፡ በዘመኑ ኹሉ፡ ተጠብቃ ወደምትኖርበት ሥፍራ፡ ወደበረሀ ትበርር ዘንድ፡ እንደታላቁ ንስር የኾነ ኹለት ክንፍ ተሰጣት። አውሬውም፡ እየበረረ ተከተላት፤ አሳደዳትም። ሊደርስባት ባለመቻሉ፡ ማዕበሉ ያጥለቀልቃት ዘንድ፡ ከአፉ፡ ታላቅ ወንዝን የሚያህል ኸረትን፡ ከአፉ አውጥቶ፡ በዚችው ሴት ላይ፡ ከወደኋላዋ አፈሰሰባት። ነገር ግን፡ ምድር፡ ሴቲቱን ረዳቻት፤ አውሬው፡ ከአፉ አውጥቶ ያፈሰሰባትን የውኃ ማዕበል፡ አፏን ከፍታና አስፍታ ውጣላታለችና። ለሴቲቱ፡ ክንፍ እንደተሰጣት፡ አውሬው፡ አላወቀ ኖሮ፡ በእርሷ፡ እጅግ ተቆጥቶ፡ ከዘሯ የተረፉትን ልጆቿን፥ የእግዚአብሔርንም ሥርዓት የሚጠብቁትን፥ በኢየሱስ መሲሕ እውነትም የሚኖሩትን ሊዋጋቸው ኼደ። ይኸው አውሬ፡ በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ።"*

ይህም ማለት፡ "ስለዚህ፡ ያ ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶች ያሉት ዘንዶ፡ ኢትዮጵያን፡ ከነልጆቿ፡ አጥለቅልቆ ለማስጠም፡ ወንዝን የሚያህል የማዕበል ውኃን፡ ከአፉ ተፍቶ አፍስሶባት፡ ሊያጠፋት ባለመቻሉ፡ ቍጣው ነድዶ፡ 'የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፥ በኢየሱስ መሲሕ እውነትም የሚኖሩትን፥ ከዘርዋ የቀሩትን'፡ እነዚህኑ፡ የኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም፡ የቃል ኪዳን ልጆቿ የኾኑትን፡ የኢትዮጵያን ሰዎች ሊዋጋ፡ እነሆ፡ በባሕር አሸዋ ላይ ቆሟል። አንተም፡ ራሱን ቀጥቅጠህ አዳንሃቸው።' ተብሎ የተተረጐመው፡ ይህ የትንቢት ቃል ነው።

በዚህ የመለኮት ቃል መሠረት፡ "'ንጉሥ ነህ!' የተባለው እግዚአብሔር"፡ **ኢየሱስ መሲሕ** ነው። **"ኢትዮጵያ"** የተባለችው፡ ንግሥት እናቱ፡ **እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም** ናት። **"'ከዘርዋ የቀሩት' ልጆቿ"** የተባሉት፡ **በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ጸንተው የሚገኙት፡ የቀደሙትና የዛሬዎቹ፥ የወደፊቶቹም የኢትዮጵያ ሕዝብ** ናቸው። **"እባብ፥ ዘንዶ፥ አውሬ"**፡ የተባለው፡ **ዲያብሎስ** ነው። **"ሰባት ራሶቹና ዐሥር ቀንዶቹ"**፡ የተባሉት፡ *ቀድሞም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፡* **የእግዚአብሔር** *መንግሥት* **የኾነችውን ኢትዮጵያን** *ለማጥፋት* **የተነሡትና የሚነሡት፡** የእርሱ [የዲያብሎስ] *መሰሎችና ተባባሪዎች፥ አገልጋዮችና መሣሪያዎች* የኾኑት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በሓሳዊው [ሓሰተኛው] *ሥጋዊና መንፈሳዊ ዕውቀታቸውና ጥበባቸው፥ ገንዘባቸውና ሀብታቸው፥* ጦር *ኃይላቸውና መሣሪያቸው ተማምነውና ተመክተው፥ ተመሣጥረውና* ተባብረው፡ **በዓለም ላይ የሰፈኑት፡ የሰዎች የሃይማኖት ድርጅቶች [አብያተ-ክህነት] እና *መንግሥታት* [አብያተ-ሕዝብ እና አብያተ-ምልክና]** ናቸው።

*አዎን! የኢትዮጵያ ልጆች፡* ከጥንት ጀምረው፡ እግዚአብሔርን ዐውቀውት፡ በመንፈሳዊው እና በ*ሥጋዊው ቃል*-ኪዳን የተቀበሉት፡ *"ፈጣሪያችን እና አምላካችን* ብቻ *ነህ!"* ብለው ሳይኾን፡ *"አባታችን እና እናታችን፥ ንጉሣችንና ንግሥታችን፥* ካህናችንና *ሊቀ*-ካህናታችን፥ *ሃይማኖታችንና አገራችን ጭምር ነህ!"* ብለው *መኾኑን ለማረጋገጥ፡* ከላይ፡ ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው፡ ከብሉይ ኪዳኑ *ቃል ጋር፡ ዐብሮ* የሚወሳ፡ *ተመሳሳይና ተዛማጅ* የኾነ፡ የአዲሱ ኪዳን *የምሥራች* ቃል አለ፤ ይህም፡ በካህኑ ኢትዮጵያዊ የሰላም *ንጉሥ*፡ በመልከ-ጼዴቅ ሹመት፡ የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ የታረደው፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዲያብሎስን፡ ከነሠራዊቱ፡ ድል መንሣቱ የታወጀበትና እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ሕዝባዊና ብሔራዊ፥ ክህነታዊና *መንግሥታዊ* ዓርማቸው አድርገው የኖሩት፡ **"ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!** *ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አንበሳ አሸነፈ!"* እና **"ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!** *ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"* የሚሉት፡ *መለኮታውያት* ቃላት ናቸው።

ከዚህ የተነሣ፡ ካህኑና ንጉሡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፥ አገሪቱና ንግሥቲቱም እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ **በሚመርዋት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥት ሥር* የሚተዳደሩት፡ "ለዚች አገር፡ ለኢትዮጵያና ለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላቸው፡ መብራቷም፡ በጉ ኢየሱስ መሲሕ ስለኾነ፡ ፀሓይ፥ ወይም፡ ጨረቃ፡ እንዲያበሩላቸው አያስፈልጓቸውም።"** (*መዝ.* ፸፫ [፸፬]፥ ፲፪-፲፬። *ራእ.* ፳፥ ፳፤ ፲፪፥ ፩-፲፯፤ ፳፩፥ ፳፫።)

*ለእግዚአብሔር ይቅርና፡* በዚህ *ዓለም፡ በግዘፍ ለምታበራው፡ ለፀሓይም* እንኳ ቢኾን፡ ራሷ *ፀሓይ፡ የብርሃኑ ምንጭ* ስለኾነች፥ *በዚያ ብርሃኗም፡ በምልዓት* ስለተከበበች፥ *የብርሃንና የጨለማ መፈራረቅ፡* በእርሷ ዘንድ ሊኖር ስለማይችል፡ *ለራሷ፡ "ትናንት፥ ዛሬና ነገ"* እንደሌለባት፡ *ለማንም ግልጽ ነው።*

እንደእርሷ ኹሉ፡ በደቂቃትና በሰዓታት፥ በቀናትና በሳምንታት፥ በወራትና በዓመታት፥ በዘመናትና በዐውዳተ-ቀመራት አቈጣጠር አማካይነት፡ እርሷ፡ ለሌሎቹ ፍጡራን የምታስገኛቸው፡ እነዚያ፡ *"ትናንት፥ ዛሬና ነገ"፡* **በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ልጆች ህልውና ዘንድ፡** ምንጊዜም፡ ነባር *ዕውቅናና* ቦታ ሳይኖራቸው፡ በምትሓታዊ ታሳቢነታቸው ብቻ ሲነገሩ ይሰማሉ። *የዓለሙ* ብርሃንና ጨለማ፤ *የጊዜው፡ ደቂቃና ሰዓት፤ የዕለቱ፡ መዓልትና ሌሊት፤ የወራቱ፡ መጸውና ጸደይ፥* በጋና ክረምት የሚፈራረቁበት፡ *የዓመቱ ዑደት* [ዙረት] የሚያልቀው፥ እንደገናም የሚጀምረው፡ *የሥጋና የምድር፥ የዓለምና* የሰው ወገኖች ለኾኑ ፍጡራን ብቻ እንጂ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንተው ለሚኖሩ፡ **ለኢትዮጵያ ልጆች** አይደለም።

እኒህ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ከእግዚአብሔር በመወለዳቸው፡ እንደቀደሙት መልከ-ጼዴቅና ንግሥት ማክዳ፣ እንደኋለኞቹም፡ ድንግል ማርያምና ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ልጆች፥ ነጋሢዎችና ካህናት [አገልጋዮች] ኾነው፡ በእግዚአብሔር አብወእም መንፈስና እውነት፥ በልጃቸው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የትንሣኤ ሕይወትና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሰንበታዊ ሥርዓት የሚኖሩ ናቸው። (አሞ. ፱፥፯። ዮሓ. ፩፥ ፲፪-፲፫።)

በዳዊት መዝሙራት፡ "**ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር! [ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!]** የተባለችው ቅድስት አካልና ባሕርይ፡ **ድንግል ማርያም** ናት። **ኢትዮጵያዊው ነቢይ ኤርምያስም፡ "ይዌልጥኑ ኢትዮጵያዊ፡ ማእሶ፥ ወነምርኒ፡ ኀበሪሁ!?** በውኑ ኢትዮጵያዊ፡ መልኩን፥ ነብርም፡ ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን!" ብሎ፡ የተናገረለት፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው። እንዲህ ከኾነ፡ **ድንግል ማርያም** እና ኢየሱስ መሲሕ፡ ለፍጹምነት ያበቁት ኢትዮጵያዊነት፡ የእግዚአብሔር ሥራ ስለኾነ፡ እውነት ነው። ስለዚህ፡ ሃይማኖት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ እውነተኞች ሰዎች፡ ሕይወት አድርገውት ይኖሩታል። እነዚህም፡ የኢትዮጵያ ልጆች ይባላሉ። (መዝ. ፷፯ (፷፰)፥ ፴፩። ኤር. ፲፫፥ ፳፫።)

እንግዲህ፡ **ኢትዮጵያዊነት፡ የእግዚአብሔር እውነት፥ ሃይማኖትና ሕይወት** ስለኾነ፡ በግል፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ፥ በኅብረብሔርነትና በሕዝብነት፥ በአገርነትና በመንግሥትነት፡ አኹን ለምንገኝበት ህልውናችን፥ ለወደፊቱና ለዘለዓለሙም፡ በዓለም-ዐቀፍ ደረጃ ሳይቀር፡ በፍጹም ነጻነት፡ አንድ ኾነው የሚኖሩትና የሚኖሩበት ሥርዓት ኾኖ፡ እነሆ፡ ዘንድሮም፡ በእናታችን እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ቸርነትና በረከት፡ ለሰባት ሺህ፡ አምስት መቶ ዘጠነኛ ዓመት ዕድሜው በቅቷል።

ባለፈው ዓመት፡ በተከታታይነት፡ የመጨረሻ ኾኖ፡ ይፋ ከወጣው፡ ከ፲፩ኛው የዐዋጅ ቃል በፊት፡ ቀደም ያለውን፡ ፲፫ኛውን [የዐዋጅ ቃል] መሠረት አድርጎ የተዘጋጀው፡ የ፳፻፱ [የ፪ሺ፱] ዓመተ-ምሕረት የቀን መቍጠሪያም፡ ለዚሁ ዕድሜ መታሰቢያነት፡ በዐውደ-ዓመቱ ቀርቧል።

ስለዚህም፡ **መስከረም ፩ ቀን፡-**

-ምናልባት፡ በእየራሳችን ድክመትና ስሕተት፥ ጕድለትና ጥፋት፡ ያሳደፍነውና ያበላሸነው፥ ያሰነካከልነውና ያስረጀነው፡ አካላዊና ባሕርያዊ የኾነ፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና አምልኮአዊ የምንዝርና ግብር ቢኖር፡ ያን ኹሉ ርኵሰት፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ፈጽመን፡ ከሰውነታችን በማስወገድ፡ ወዲያ አውጥተንና አሽቀንጥረን ጥለን፣ ኹለንተናችንን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች አንጽተን ያደስንባት፣

-ከዚህም ጋር፡ ለእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና ለልጇ ለወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓላት ክብር፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ቅዱስ ቊርባናችን በኾነው፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን የምናበቃባት፣

-ሰላማችንን ያስገኘልን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ድኅነትን ካስገኘችልን፡ ከእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ በቅዱሱ ኪዳን የተጐናጸፍነውንና የተቀዳጀነውን፡ የዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደአዲስ ተሿሚና ተሸላሚ ባለድል የተቀበልንባት፣

-ከአሮጌው፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ትንሿን ትርፍ የጳጕሜን ወር፡ በንስሓ፥ በጋድ ጾምነትና ንኡስ ሱባዔነት፡ የምስጋና ጾምና ጸሎት አድርገን ያሳለፍንላት መኾኗ ሊዘከር [ሊታሰብ] ይገባል።

# የዐውደ ዓመቱ፡ የምሥራች መልእክት።

በመስከርም ፩ ቀን፡ እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ ምድር በከለላት፡ በኤዶም ገነት፡ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ፥ የቅዱሱ ኪዳን መጀመሪያና መነሻ፥ መሠረትና ምንጭ የኾነውንም፡ ሥርዓተ-ጋብቻን፡ በእነርሱ [በአዳም እና በሔዋን] ሰውነት፡ እውንና ሕያው አድርጎ፡ ፍጥረቱን፡ እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ፡ ሥልጣኑንና ችሎታውን በሰጣቸው ጊዜ፡ እነሆ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለግዙፉ ዓለም ተገለጠች። እርሷም፡ በቀደመው የፍጥረት ዘመን፡ የክፉው ወገን ከኾኑት፡ ከሰዎች ልጆች ተለይተው፡"የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እስከዛሬ የኖሩባት፥ ዛሬም፡ እየኖሩባት ያሉ፥ በፍጻሜ የሕይወት ዘመንም፡ ንጉሡ እግዚአብሔር፡ "ንዑ ኀቤየ! ቡሩካኑ ለአቡየ! ትረሱ መንግሥተ-ሰማያት፣ ዘድልው ለክሙ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። እናንት የአባቴ ቡሩካን! ወደእኔ ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ የተዘጋጀችላችሁ፡ በሰማያት ያለችው መንግሥት፡ ይህቻትላችሁ ውረሷት! ተብለው፡ የጥንት ጠላቶቻቸው፡ የክፋትና የሓሰት፥ የኃጢአትና የሞት አበጋዞች፡ ዲያብሎስና ጭፍሮቹ፡ ፈጽመው በተደመሰሱበት፣ "ወእምዝ ርኢኩ ፡ ሰማየ ሐዲሰ፥ ወምድረ ሐዳሰ፡ እስመ ሰሰለ ሰማይ ቀዳማይ፤ ወምድርኒ ቀዳሚት። ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር ዐልፈው፡ አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር የተተኩበት" የቀደመው አሮጌ ብልሹ ሥርዓት፡ ተሽሮና ተወግዶ፡ ዘለዓለማዊው የሙሽርነት ሥርዓት በሰፈነበት አዲስ ሕይወት የሚኖሩባት ናት።

የዚች መለኮታዊት መንግሥት ተቃዋሚ የኾነው እባቡ፥ ዘንዶውና አውሬው ዲያብሎስ፡ እስካኹን እንዳደረገውና ዛሬም እንደሚያደርገው ኹሉ፡ ረቂቅ የክፋት መርዙን፡ "አዳም እና ሔዋን" በተባሉት፡ በመጀመሪያዎቹ ሰዎች ህልውና ላይ ረጭቶ፡ ባደረሰው የጥፋት ርኵሰት፡ አስቀድሞ፡ "ደቂቀ እግዚአብሔር [የእግዚአብሔር ልጆች]" ተብለው ከሚጠሩት፡ የአቤል ዘሮች ከኾኑት፡ ኖኅንና ሓይከልን፥ መልከ-ጼዴቅንና ሳሌምን፥ አብርሃምንና ሣራን፥ ኬጡራንና ዮቶርን፥ ሙሴንና ሲጳራን፥ ዳዊትንና ቤትሳባን፥ ሰሎሞንንና ማክዳን ከመሰሉት፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ወገኖች የተለዩት የቃኤል ዘሮች፡ "የሰው ልጆች" ተብለው፡ ለ፸ሺ፭፻ ዓመታት፡ የእየራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ ያስከትለባቸውን፡ የመርገም ፍዳ ተቀባዮች ኾነው ኖሩ!

የተወሰነው፡ ይህ ዘመነ ኵነኔ ሲፈጸም፡ ቀድሞ፡ "በከመ ሢመቱ፡ ለመልከ-ጼዴቅ! በመልከ-ጼዴቅ የሹመት ሥርዓት!" ተብሎ የተነገረለት፥ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ! የይሁዳው ነገድ አንበሳ አሸነፈ!" የተባለው፡ ድል አድራጊው፡ <u>ሰላማችን</u>፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ ዘለዓለማዊው ሊቀ-ካህናትና እውነተኛው ንጉሠ-ነገሥት ኢየሱስ መሲሕ፣ ቀድሞ፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር! ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" ተብሎ፡ በነቢያት ከተነገረላት፥ ኋላም፡ "ወላዲተ-አምላክ፣ የአምላክ እናት" ለመኾን ከበቃችው፥ በመጨረሻም፡ እኛ፡ "ደቂቀ-ኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ ልጆች" የተባልን ልጆቿ፡ "እምነ ጽዮን! እናታችን ጽዮን!" እያልን ከምንጠራት፡ ከኢትዮጵያዋ እናት ንግሥታችንና ምድረ-ርስት አገራችን፥ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችንና የዘለዓለምም መቅደሳችን ከኾነችው፡ ከ<u>መድኃኒታችን</u>፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ የዛሬ ፪ሺ፱ ዓመት ተወልዶ፡ ዘመነ-ምሕረትን አስገኘ። ተወልዶም፡ በዲያብሎስ ረቂቅ ተንኰልና በሥጋ ባሕርይ ድክመት ምክንያት፡ በሰው ልጆች ላይ፡ ተንሰራፍተው የኖሩትን፡ ክፉትንና መርገምን፥ ኃጢአትንና ሞትን በማስወገድ፡ በድል አድራጊነት፡ የዘለዓለም ሰላምን፡ ለፍጥረቱ ኹሉ አጐናጸፈ።

ይህን ፍጹም ጸጋ ለመቀበል፡ "እንቢ!" ላሉት የሰው ልጆችም፡ "**ሑሩ እምኔየ ርጉማን! ውስተ እሳት ዘለዓለም! ዘድልው ለሰይጣን፥ ወለመላእክቲሁ።** *እናንተ ርጉማን! ከእኔ ወግዱ! ለሰይጣንና ለጭፍሮቹ ወደተዘጋጀው፡ ወደዘለዓለም እሳት፡ ኺዱ!"* የሚለውን የፍርድ ቃል፡ ለዳግም ምጽአቱ አቆይቶላቸዋል።

እነዚህ ዘመናት፡ ማለትም፡ ዘመነ-ኵነኔውና ዘመነ-ምሕረቱ ሲጠቃለሉ፡ ለቀረው ፍጥረት፡ ድምሩ፡- ፯ሺ፭፻፱ ዓመታት የኾነውን፡ ዓመተ-ዓለም፣ ለእኛ፡ **ለኢትዮጵያ ልጆች** ግን፡ ፯ሺ፭፻፱ ዓመታት የኾነውን፡ <u>ዓመተ-ኪዳን</u> ያስገኛሉ።

ስለዚህ፡ በዚች፡ በመስከረም ፩ ቀን፡-

፩ኛ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን፡ የ፯ሺ፭፻፱ኛውን ዓመተ-ልደቷንና የነጻነት ህልውናዋን በዓል፥**

፪ኛ፡ የአዳምና የሔዋንን ልደት፥ እንዲሁም፡ ሰባቱን ቃል-ኪዳናት ያካተተው፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ መሠረትና መነሻ የኾነው፡ "ኪዳነ አዳም ወሔዋን" የተባለው ሥርዓተ ጋብቻ የተመሠረተበትን ትንግርት ያጠቃለለውን፡ **የ፯ሺ፭፻፱ኛውን ዓመት፡** የፍጥረትን መገኛ በዓል፥

፫ኛ፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻት፡ የአምላክ እናት፡ ድንግል ማርያም የተወለደችበትን፡ **የ፪ሺ፳፭ኛውን ዓመት** በዓል፣

፬ኛ፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእርሷ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም እናቱ የተገኘበትን፥ "ዓመተ-ምሕረት"ም የባተበትን፡ **የ፪ሺ፱ኛውን ዓመት፡** የልደቱን በዓል፡ እነሆ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ በታላቅ ደስታና ሓሤት፥ በልዩ ሥጋዊ፥ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ሥርዓትና ድምቀት፡ በሰማያትና በምድር ያከብሩታል።

ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ **ይህን፡ ታላቁን፡ የዐውደ-ዓመት በዓላቸውን፡ ከመስከረም ፩ ቀን አንሥተው፡ ሕፃን ኢየሱስ መሲሕ፡ በተወለደ በ፵ ቀኑ፡ ወደቤተ-መቅደስ እስከገባበት፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ድረስ፡ በያሉበት፡ በፋሲካ ሙሉ ዝግጅትና በፍጹም ኹለንተናዊ ደስታ በማክበር፡** ለዚህ ላበቃቸው ቸሩ ፈጣሪያቸው፡ የተለመደ ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ።

(ዘልደት [ዘፍጥ.] ፮፥ ፪፤ ፲፬፥ ፲፰-፳፬። ማቴ. ፳፭፥ ፴፫-፴፬። ዕብ. ፭፥ ፭-፲፤ ፯፥ ፩-፳፰። ራእ. ፳፩፥ ፩-፬።)

\+ \+ \+

**(ገጹ ይቀጥላል)**

# የታላቁ ዐውደ ዓመት በዓል
# ምንባባትና መዝሙራት።

መስከረም አንድ ቀን፡ በርእሰ ዓውደ ዓመት፣
በድንግል ማርያም፡ በእናቲቱ ልደት፣
በኢየሱስ መሲሕ፡ ባምላክ ልጁም ትስብእት፣
የተወረሰውን፡ ዓመተ-ምሕረት፣
በአዳምና ሔዋን፡ የዓለሙን ፍጥረት፣
በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያን ነጻነት፣
የተላበሱባት፡ በእግዚአብሔርዋ መንግሥት፣
ኢትዮጵያውያን፥ ደግሞም፡ ኢትዮጵያውያት፣
ባሉበት ቦታና በኑሮአቸው ዓይነት፣
በግል፥ በቤተሰብ፥ በኅብረሰብነት፣
ቤተ-ክርስቲያናቸው፡ መካነ-ኪዳናት፣
በቅዱሱ መንፈስ በተሰበሰቡበት፣
በዝርጉ እጆቻቸው፡ የታየው ምልክት፣
የመስቀል ማኅተም፡ ኾኗቸው አብነት፣
በ፬ቱ ማዕዝናት፡ በሚፈጸም ሥርዓት፣
ለታላቁ በዓል፡ ግጻዌው ወጥቶለት፣
ይኸው ያቅርቡበት፡ የምስጋናን መሥዋዕት።

\+ + +

## ፩ኛ፡ በምዕራቡ ማዕዘን የሚካኼድ፡ ሥርዓተ ቅዳሴ፤
## ስለፍጥረት ልደት እና ስለርእሰ-ዓውደ-ዓመተ-ምሕረት።

**ምንባብ፡-**

ሮሜ ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፰-፲፬፤
ራእ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፩-፰፤
ሓዋ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፲፱-፳፮።

**ምስባክ፡-** መዝ. ፷፬፥ ቁ. ፲፩-፲፪፤

| | |
|---|---|
| ወትባርክ፡ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ፤ | የምሕረትህን ርእሰ ዓውደ ዓመት፡ ትባርካለህ፤ |
| ወይጸግቡ፡ ጠላተ ገዳም፤ | ምድረ-በዳው፡ በልምላሜ ይሸፈናል፤ |
| ወይረውዩ፡ አድባረ-በድው። | የበረሀ ተራሮች፡ በዝናብ ይረካሉ። |

**ብሥራት [ወንጌል]፡-** ሉቃ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፲፬-፳፱።

## ፪ኛ፡ በሰሜኑ ማዕዘን የሚካኼድ፡ ሥርዓተ ቅዳሴ፤
## ስለቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ፡ ልደትና ነጻነት።

**ምንባብ፡-**

ዕብ. ምዕ. ፮፥ ቁ. ፩-፲፤
ራእ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፲፤
ሓዋ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፳፮-፴፱።

**ምስባክ፡-** መዝ. ፷፯፥ ቁ. ፴፩-፴፪፤

| | |
|---|---|
| ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር! | ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች! |
| ነገሥተ-ምድር፡ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር! | የምድር መንግሥታት፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ! |
| ወዘምሩ ለአምላክነ! | ለአምላካችን፡ ዘምሩም። |

**ብሥራት [ወንጌል]፡-** ማቴ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፴-፵፪።

## ፫ኛ፡ በደቡቡ ማዕዘን የሚካኼድ፡ ሥርዓተ ቅዳሴ፤
## ስለእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የትስብእት ልደት።

**ምንባብ፡-**

ዕብ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፫፤
ራእ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፫-፲፱፤
ሓዋ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፮-፲፬።

**ምስባክ፡-** መዝ. ፻፴፩፥ ቁ. ፲፫-፲፬፤

| | |
|---|---|
| እስመ ኀረያ እግዚአብሔር፡ ለጽዮን፤ | እግዚአብሔር፡ ጽዮንን መርጧታልና፤ |
| ወኣብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤ | ማደሪያውም ትኾነው ዘንድ፡ ወዷታል፤ |
| ዛቲ ይእቲ፡ ምዕራፍየ ለዓለም። | "ይህች፡ ለዘለዓለም፡ ማረፊያዬ ናት!" አለ። |

**ብሥራት [ወንጌል]፡-** ሉቃ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፳፮-፶፮።

## ፬ኛ፡ በምሥራቁ ማዕዘን፡ ከፍሬ ቅዳሴ ጋር የሚካኼድ፡ ሥርዓተ ቅዳሴ፤
## ስለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የትስብእት ልደት።

**ምንባብ፡-**

ገላ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፩-፯፤
፩ዮሐ. ምዕ. ፬÷ ቁ. ፩-፲፫፤
ሐዋ. ምዕ. ፲፫÷ ቁ. ፲፮-፴፫።

**ምስባክ፡-** መዝ. ፪÷ ቁ. ፯-፰፤

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔር ይቤለኒ፡- "ወልድየ አንተ! | እግዚአብሔር አለኝ፡- "አንተ፡ ልጄ ነህ! |
| "ወአነ፡ ዮም ወለድኩከ! | "እኔ፡ ዛሬ ወለድሁህ! |
| "ሰአልከ እምኔየ፤ ወሀብኩከ አሕዛበ፡ ለርስትከ!" | "ጠየቅኸኝ! አሕዛብን፡ ርስት አድርጌ ሰጠሁህ።" |

**ብሥራት [ወንጌል]፡-** ሉቃ. ምዕ. ፪÷ ቁ. ፩-፳።

## የልደት ዝማሬ

**በጎል ሰከበ! በአጽርቅት ተጠብለለ!**
**ቤዛ ኵሉ ዓለም! ቤዛ ኵሉ ዓለም! ዮም ተወልደ!** *(፪ ጊዜያት)*

ትርጉም

**አምላክ፡ ሰው ኾኖ፡ ዓለሙ ኹሉ ሊያድን፡ ዛሬ ተወለደ ለእኛ!**
**በጨርቅ ተጠቅልሎ፡ በበረት ውስጥ ተኛ!**

---

**አንፈርዐፁ ሰብአ ሰገል!** *(፪ ጊዜያት)*
**አምኃሆሙ፡ አምጽኡ መድምመ።** *(፪ ጊዜያት)*

ትርጉም

**ሊሰግዱላቸው፡ ድንቅ የኾነ ገጸ-በረከታቸውን ይዘው የመጡት፡ የሰገል ሰዎች፡**
**በሕፃኑ ኢየሱስ መሲሕ እና በእናቱ ድንግል ማርያም ፊት፡ በደስታ ጨፈሩ!**

---

**አማን፡ በአማን! አማን፡ በአማን!** *(፪ ጊዜያት)*
**መንክር፡ ስብሓተ ልደቱ! መንክር፡ ስብሓተ ልደቱ!** *(፪ ጊዜያት)*

ትርጉም

**እውነት፡ በእውነት! እውነት፡ በእውነት!**
**የመሲሕ ኢየሱስ፡ የልደቱ ገናንነት፡ ዕፁብ ድንቅ ነው!**

---

# <u>የምሥራች ሰላምታ</u>

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከባዓለ-ግዝረቱ፥ ከዚያም፡ እስከበዓለ በአተ-መቅደሱ ድረስ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ እርስ በእርሳቸው የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፡-

<u>ከመስከረም ፩ እስከ፳ ቀን፡-</u>

| | |
|---|---|
| "ዮም ፍሥሓ ኮነ!" | "በእንተ በዓለ ልደተ-ፍጥረት!" |
| "ዮም ፍሥሓ ኮነ!" | "በእንተ ልደተ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር!" |
| "ዮም ፍሥሓ ኮነ!" | "በእንተ ልደተ ትስብእታ፡ ዘእግዝእትነ፥ ወመድኃኒትነ ድንግል ማርያም!" |
| "ዮም ፍሥሓ ኮነ!" | "በእንተ ልደተ ትስብእቱ፡ ዘእግዚእነ፥ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ!" |

<u>ትርጉም</u>

| | |
|---|---|
| "ዛሬ የደስታ ቀን ነው!" | "አዎን! ፍጥረት፡ በፈጣሪ የተገኘበት የመታሰቢያ በዓል ነውና!" |
| "ዛሬ የደስታ ቀን ነው!" | "አዎን! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የተገለጠችበት የነጻነት በዓል ነውና!" |
| "ዛሬ የደስታ ቀን ነው!" | "አዎን! እግዚአብሔር እናታችንና መድኃኒታችን ድንግል ማርያም፡ በሰውነት የተወለደችበት በዓል ነውና!" |
| "ዛሬ የደስታ ቀን ነው!" | "አዎን! እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰውነት የተወለደበት በዓል ነውና!" |

<u>ከመስከረም ፱ እስከጥቅምት ፱ ቀን፡-</u>

| | |
|---|---|
| "ዮም ፍሥሓ ኮነ!" | "በእንተ ግዝረቱ፡ ዘእግዚእነ፥ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ!" |
| "ዛሬ የደስታ ቀን ነው!" | "አዎን! እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰውነቱ የተገረዘበት በዓል ነውና!" |

<u>በጥቅምት ፲ ቀን፡-</u>

| | |
|---|---|
| "ዮም ፍሥሓ ኮነ!" | "በእንተ በአተ-መቅደሱ፡ ዘእግዚእነ፥ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ!" |
| "ዛሬ የደስታ ቀን ነው!" | "አዎን! እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደቤተ-መቅደስ የገባበት በዓል ነውና!" |

ይህ የነፍስ፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ የደስታና የምስጋና መገለጫ፡ በትንሣኤ የፋሲካ ሥርዓትና ዝግጅት፡ ከመስከረም ፩፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ድረስ ይቀጥላል።

\+ \+ \+

# ርእሰ ዐውደ ዓመት።

"የዓመቱ በዓላት ዘውድ" የኾነው፡ ታላቁ በዓላችን፡ በመስከረም ፩ ቀን የሚውለው ነው። ስለዚህ፡ "ርእሰ ዐውደ ዓመት" ይባላል፤ የብሉይ ኪዳኑ ነቢያት፡ መጨረሻና የአዲስ ኪዳኑ ሓዋርያት፡ መጀመሪያ ከኾነው፡ ከመጥምቁ ዮሓንስ የተነሣም፡ "ቅዱስ ዮሓንስ"፥ ከዘመነ ኰነኔ፡ ወደዘመነ ምሕረት የተሸጋገርንበት፥ እንዲሁም፡ አሮጌው ዓመት ዐልፎ፡ አዲሱ ዓመት የሚተካበት በመኾኑም፡ "የዘመን መለወጫ"፥ ደግሞም፡ የእግዚአብሔር ሙሽሪት ንግሥትና የፍጥረተ-ዓለሙ መድኃኒት የኾነችው፥ ኢትዮጵያዋ  ድንግል ማርያም፡ ድል አድራጊውንና እውነተኛውን፡ ዘለዓለማዊ የሰላም ንጉሥ የኾነውን፡ ሕፃን ኢየሱስ መሲሕን በመውለዷ፡ ከፍጡራኖቿ የቀረቡላትን የከበሩ የዐራስ ጥሪ፡ ምሥራች ገጸ-በረከቶች [ስጦታዎች] ለማዘከር፡ "ዕንቍጣጣሽ!" በምንላቸው፤ የስም አጠራሮችም ይታወቃል። እነዚህ ስያሜዎች፡ ለዚች ዕለት፡ ለምን እንደተሰጡ፡ ከዚህ የሚከተሉት አጫጭር መግለጫዎች፡ በበለጠ ያስረዳሉ።

ሀ. በአኹኑ ጊዜ፡ በዓለማውያን ሰዎች ተከልላ በተወሰነችው፡ በአገራችን ምድረ-ኢትዮጵያ፡ "ክረምት" የምንለው፡ የዝናቡ ወራት ዐልፎ፡ የአበባው፥ የልምላሜውም ወራት ሲተካና በደመና ተሸፍኖ የከረመው ሰማይ ጠርቶ፡ በዕሓይ ብርሃን ሲደምቅ፡ "መስከረም ጠባ!" እንላለን። በዚህ ጊዜ፡ የሚሰማን ደስታ፡ አፍኣዊ ብቻ ሳይኾን፡ ውሳጣዊም፥ መንፈሳዊም ስለኾነ፡ በቃላት ሊገለጽ ያዳግታል። ወራቱ ተለውጦ፡ በብርሃን ፀዳል ሲመላ፥ ዘመኑ፡ በአዲስ፡ ያውም፡ በምሕረት ዓመት ሲተካ፡ የእኛም መንፈስ ዐብሮ፡ በደስታ ብርሃን ይፈካል፤ አእምሮአችንም ይታደሳል።

"አዎን! አሮጌው ዘመን ዐልፎ፡ አዲሱ ሲተካ፡ "መስከረም ጠባ! ፀሓይ ወጣ!" ብለን፡ የአዲሱን ዓመት፡ የሥጋዊ ዕድሜ ጕዞ፡ በሥነ ፍጥረት እንጀምራለን፤ እንደዚሁ ኹሉ፡ በአዳምና ሔዋን፡ የኃብቻ ቃል-ኪዳን ተወጥኖ፡ በዳግማዊው አዳም ኢየሱስ መሲሕና በዳግማዊቷ ሔዋን ድንግል ማርያም፡ የምሕረት ቃል ኪዳን የተፈጸመውን፡ የዓመቱን መንፈሳዊ የሕይወት ጕዟችንን "ዑደት" {ዙረት]፡ መስከረም ፩ ቀን በሚውለው ዕለት እንጀምራለን፤ ስለዚህ፡ ዕለቲቱን፡ በዚህ ገጽታዋ፡ በዓል አድርገን ስለምናከብራት፡ "የዓመቱ ዙረት መነሻ ናት!" ለማለት፡ "ርእሰ ዐውደ ዓመት" ትባላለች።

"ዖደ" በግእዝ፡ "ዞረ" ማለት ሲኾን፡ "ዐውድ"፡ "መዞሪያ" ማለት ነው። ያለፈው፡ የዓመቱ ዙረት፡ በ፫፻፷፭ ቀኖች ተሩብ ውስጥ አልቆ፡ አዲሱ ዙረት፡ የተጀመረ መኾኑን ለማስታወቅ፡ ይህችን ቀን፡ "ርእሰ ዐውደ ዓመት" ብለን እናከብራታለን። "መዞር"፡ መሽከርከርን፥ ወይም፡ ክብ የኾነ መስመርን ተከትሎ መጓዝን ስለሚያሳይ፡ ይህን ቀን፡ በዘመናዊው የሥነ ዕውቀት (science) አነጋገር፡ "'መሬት፡ ፀሓይን፡ አንድ ጊዜ ዞራ ዐብቅታ፡ አዲሱን ዙረቷን፡ እንደገና የምትጀምርበት ዕለት!' ይባላል!" ማለት ነው።

ይህች መስከረም ፩ ቀን፡ የፈጣሪ ዕፁብ ድንቅ ሥራ የኾነው ሥነ-ፍጥረት የተጀመረባትን ዕለት ለማዘከር፡ የተመደበች ናት፤ በዚች ዕለት፡ የቤተ-ክህነቱ ሊቆቻችን፡ የሥነ-ፍጥረት በረከቶች ኾነው፡ ከቸሩ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች ሥጋዊ ኑሮና መንፈሳዊ ሕይወት፥ ለቍርባንና ለመሥዋዕትም፡ እንደሚያስፈልጋቸው ዐውቆ፡ በእየዓመቱ፡ ከምድር አብቅሎ ከሰጣቸው ሲሳያት መካከል፡ ለዓይነት፡ ከአዝርዕቱ፥ ከአትክልቱና ከዕፀዋቱ፡ የስንዴን፥ የወይንንና የጽጌያትን ፍሬዎች፥ ዕጣኑና ጧፉ ሳይቀር፡ በመሶበ ወርቅ ኾኖ፡ የዕንቍጣጣሽ አበባ ጕንጕንን ጭምር፡ ለበረከት ያህል፡ በቤተ መቅደስ ያስቀርባሉ።

እነዚህ ኹሉ፡ ተደርድረው በሚታዩበት፥ ካህናቱና ሕዝቡም፡ ጸጥ ብለው በተቀመጡበት፡ ስለለጋሡ ቸር ፈጣሪና ስለተለጋሾቹ ፍጡራን፥ በጠቅላላ፡ ስለሥነ-ፍጥረት፥ ስለጊዜ አሰላልና ስለዘመን አቈጣጠር፡ ማለትም፡ ስለካልዕት፤ ስለደቂቃና ስለሰዓት፥ እንዲሁም፡ የ፳፬ ሰዓቶች አንድ ቀንን፥ ወይም፡ እያንዳንዳቸው፡ ፲፪ ሰዓቶች ያሏቸውን፡ እኩሌቶቹን መዓልትንና ሌሊትን ስለሚያስገኘው ስለኬክሮስ፥ ስለዕለታትና ስለሳምንታት፥ ስለወራትና ስለዓመታት፥ በጠቅላላ፡ ስለዘመናት፡ በቃላቸው አስፋፍተውና አብራርተው፥ ተንትነውና ዘርዝረው ያሳውቃሉ።

"ዐውደ-ዕለት"፥ "ዐውደ-ወርኅ"፥ "ዐውደ-ዓመት"፥ "ዐውደ-አበቅቴ"፥ "ዐውደ-ማኅተም"፥ "ዐውደ-ቀመር" እና "ዐውደ-ፀሓይ" በተባሉት፡ በሰባቱ የጊዜ መሥፈሪያዎች፡ የዓመቱን የቀን መቍጠሪያ ያወጣሉ። እንዲሁም፡ "አበቅቴ" እና "መጥቅዕ" በተባሉ፡ የቍጥር ማስሊያ መደቦች፡ የዓመቱ፡ አጽዋማት [የጾም ቀኖች] የሚጀምሩበትንና የሚያበቁበትን፥ የዓመቱም በዓላት የሚውሉበትን ዕለትና ወር ያስታውቃሉ። ሊቃውንቱ፡ ይህን፡ "ባሕረ-ሓሳብ" የሚባለውን፡ ጥልቅ የሒሳብ ሥራ፡ ስሌቱንና አቀማመሩን አከናውነው፡ ለቤተ-ሕዝቡና ለቤተ-ምልክናው አባሎች ኹሉ፡ በይፋ የሚያሰሙት፡ እዚያው፡ በቤተ-መቅደሱ መድረክ ላይ በሚካኼደው ጉባኤ መካከል ቆመው፡ በቃላቸው ስለኾነ፡ የአእምሮ ንቃታቸው ያስደንቃል።

ስለእኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የዘመን አቈጣጠር ጥንታዊነት፥ ብቸኛ ልዩነትና ትክክለኛነት፥ ከሌሎቹም፡ የዓለም ሕዝቦች፡ የአቈጣጠር ስልት፡ ስለሚለይበት ኹኔታ፡ የሚያብራራው ዝርዝር ሓተታ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፍ ውስጥ ይገኛልና፡ ያንን መመልከት ነው። [በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. በንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ የተዘጋጀ፤ ገጽ ፩፻፴፰-፲፻፶፫።]

በ. "ናሁ፡ አነ እፌኑ መልአክየ ቅድመ ገጽከ፤ ዘይጸይሕ ፍኖተከ! ቃለ ዐዋዲ፤ ዘይሰብክ በገዳም፤ ወይብል፡- 'ጺሑ ፍኖተ-እግዚአብሔር! ወዐርዩ መጽያሕቶ!' እነሆ፡ መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛዬን፡ በፊትህ እልካለሁ፤ 'የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ! ጥርጊያውንም አስተካክሉ!' እያለ፡ በምድረ-በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ!" ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ፡ ስለኤልያስ የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም የመጣውን፡ መጥምቁ ዮሓንስን ለማስታወስ፡ የዚች ዕለት በዓል፡ "ቅዱስ ዮሓንስ"ም ይባላል።

እግዚአብሔር ወልድ፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ ሰው ኾኖ በመወለዱ፡ "ዓመተ-ምሕረት" ለተባለው፤ ለዘመነ-ሓዲስ፡ ማለትም፡ ለአዲሱ ዘመን መግቢያ፥ ለትንቢቱና ለተስፋውም መፈጸሚያ፡ ማረጋገጫ እንደኾነ ኹሉ፡ የነቢያት መደምደሚያና የምሥራቹ ሓዋርያት መጀመሪያ የኾነው የመጥምቁ ዮሓንስ፡ የሰማዕትነት ዕረፍት ደግሞ፡ ለዘመነ ብሉይ፡ ማለትም፡ ለአሮጌው ዘመን ማብቂያ፡ ምልክት ኾነ።

ገ. የመጀመሪያዎቹ ወንድ እና ሴት፡ አዳም እና ሔዋን የተፈጠሩት፥ የጋብቻ ቃል-ኪዳናቸውንም፡ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉባት፥ ኢትዮጵያም፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ተመሥርታ፡ የነጻነት ህልውናዋን የጀመረችባት ዕለት የምትዘከርባት፥ ኖኅና ልጆቹ፡ ከጥፋት ውኃ ድነው፡ አራራት ላይ፡ ከመርከባቸው የወጡባት፥ በተለይ፡ የኋለኞቹ አዳም እና ሔዋን፡ ማለትም፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በፈጣሪ ጥበባት፡ የተገኙትን ምሥጢራት ኹሉ፡ በጥራት አጠቃልሎና አዋሕዶ፡ ለፍጹሙ መልካም ሕይወት ያበቃው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እና እናቱ፡ እግዚአብሔር-እም ቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለዱባት፡ "ዓመተ-ምሕረት"ን ያስገኘች በመኾኗ፡ በዓሏ፡ "የዘመን መለወጫ" ይባላል።

ደ. "አንትሙ፡ ለሊክሙ ሰማዕትየ፤ ከመ እቤለክሙ፡- 'አንሰ ኢኮንኩ፡ ክርስቶስሃ፤ ዳእሙ፤ ተፈነውኩ ቅድሜሁ፡ እስብክ። ዘቦቱ መርዓት፡ መርዓዊ ውእቱ። ወዐርኩሰ ለመርዓዊ፡ ዘይቀውም፥ ወይሰምዖ፡ ፍሥሐ ይትፌሣሕ፡ በእንተ ቃለ መርዓዊ፥ ወመርዓት። ወፍስሐ ዚአየሰ፡ ናሁ ተፈጸመት! እናንተ፡ 'እኔ መሲሕ አይደለሁም፤ ነገር ግን፡ እሰብክ ዘንድ፡ ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ!' እንዳልኋችሁ፡ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ። ሙሽራዪቱ ያለችው፡ እርሱ፡ ሙሽራ ነው። የሙሽራው ሚዜማ፡ ቆሞ ስለሰማው፡ ስለሙሽራውና ስለሙሽራዪቱ ቃል፡ በታላቅ ደስታ፡ ደስ ይለዋል። ይህችም፡ የእኔዪቱ ደስታ፡ እነሆ ተፈጸመች!" ብሎ፡ መጥምቁ ዮሐንስ፡ የተናገረውን ቃል እናስታውሳለን። በዚህ ቃል፡ "መርዓዊ፡ ሙሽራ" የተባለው፡ ሕፃኑ ኢየሱስ መሲሕ፡ በበረት ተወልዶ ሣለ፡ ሰብአ-ሰገል፡ እየሰገዱ፡ እጅ መንሻቸውን እንዳቀረቡለትም፡ እንዘክራለን። በዚያን ጊዜ፡ እኒሁ ሰብአ-ሰገል፡ የሙሽራው እናት ለኾነችው፡ ለዐራሲቱ ሙሽሪት፡ ለኢትዮጵያዋ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡- 'ለአንቺም፡ ዕንቈጳግዮን፡ ለጣትሽ እነሆ!" ብለው፡ ገጸ-በረከታቸውን [ስጦታቸውን] አበርክተውላት ነበር።

የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት፡ የምሥራች ደስታቸውን፡ በአንድነት በገለጹባት፡ በዚች የልደት ቀን፡ ዛሬም፡ እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የአበባ ጒንጒናችንን ይዘን፡ ስለእናት አገራችንና መቅደስ ንግሥታችን፥ ስለመድኃኒታችንም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርስ-በእርሳችን፡ ይኸው፡ "ዕንቍጣጣሽ!" እንባባላለን።(ማር. ፩፥ ፪-፫። ዮሐ. ፫፥ ፳፰-፴።)

## በበዓሉ የሚፈጸሙ፡ ሃይማኖታውያን ባህሎች።

በዚህ በዓል ጊዜ፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በግል፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ ደረጃ፡ ልንፈጽማቸው የሚገቡን፡ ሥርዓቶችና ባህሎች አሉ። ከእነዚህ መካከል፡ እስኪ፤ ዋና ዋናዎቹን እንጠቃቅሳቸው፡-

፩ኛ፡ ለመስከረም ፩ ቀን አጥቢያ፡ ገና ሌሊቱ ሳይነጋ፡ ሰው ኹሉ፡ በቤቱ፥ ወይም፡ ወደወንዝ ወርዶ፡ ገላውን፡ የመታጠብ ልማድ አለ። ይኸውም፡ "ያለፈውን ዓመት የሥጋ ዕድፍ፡ ከሰውነት ገላ ማስወገድ ብቻ ሳይኾን፡ የማይጠቅመውንና የሚጎዳውን አስተሳሰብና ነገር ኹሉ፡ ከነጓዙ ጥሎ፡ ሰውነትንም፡ የነፍስ ዕድፍ ከኾነው፡ ከኃጢኣት ጭምር አንጽቶ፡ እያንዳንዱ፥ እያንዳንዷም የኢትዮጵያ ልጆች፡ በየአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያናቸው በመገኘትና አስቀድሰው በመቁረብ፡ እየራሳቸውን፡ በኪዳነ-ምሕረቱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ማጽደቅ፥ አዲሱን የምሕረት ዓመትም፡ በጠዳው ንጹሕና ነጻ መንፈስ መቀበል ይገባቸዋል!" ማለት ነው።

፪ኛ፡ ገና በዋዜማው ማታ፡ የቤቱ ወንድ ኹሉ፡ ችቦውን ይዞ፡ ወደማድቤት እየገባ፡ በምድጃው እሳት፡ ከለኰሰ በኋላ፡ ተመልሶ ሲወጣ፡ የደጃፉን መድረክ፡ በችቦው ነበልባል ይተረኵሳል። በዚህ ጊዜ፡ እርሱም፡ ሴቶቹም፤ ወንዶቹም፡ የቤተሰቡ አባሎች፡ ድምፃቸውን እያሰሙ፡ "የጎመን ምንቸት ውጣ! የገንፎ ምንቸት ግባ!" ይላሉ። ይህም፡ "በክረምቱ ወራት፡ በብዛት፡ ለምግብ እየተቀቀለ የሚቀርበው፡ በቀላሉ፡ በዝናብ የበቀለው፡ የጓሮው አትክልትና ቅጠላቅጠል ነበረ። እንግዴህ ወዲህ ግን፡ የተዘራው፡ ጥራጥሬ እህል በቅሎ፥ አፍርቶና ተመርቶ፥ ታጭዶና ተወቅቶ፥ ወደጎተራ የሚገባበትና የሚከማችበት፥ ከዚያም፡ እየታፈሰ፡ በምግብነትና በመጠጥነት እየተዘጋጀ የሚቀርብበት ጊዜ ደረሰ!" የሚለውን፡ የምሥራች መልእክት ማሰማታቸውን ይህን የመሰለውን የሕይወት ጸጋ ለለገሣቸው ፈጣሪያቸው፡ ምስጋናቸውን ማቅረባቸው ነው።

፫ኛ፡ የችቦው መብራት፡ "የክረምቱ ዝናምና ጨለማ ዐልፎ፡ የፀሓዩ ብርሃን ወጣልን!" የሚለውን ደስታቸውን ለመግለጽ ነው።

፬ኛ፡ ጧት በማለዳው፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ የአዲሱን የምሕረት ዓመት መግባት በማብሠር፡ለየወላጆቻቸውና ለየቤተሰቦቻቸው፥ ለየቅርብ ጎረቤቶቻቸውና ለየሩቅ ዘመዶቻቸውም፡ ወደየመኖሪያ ቤቶቻቸው እየኼዱ፡ "ዕንቍጣጣሽ! እግዚአብሔር፡ እንኳን፡ ከዘመን ወደዘመን አሸጋግሮ፡ ለአዲሱ ዓመት፥ ለዐውደ-ዓመቱና ለብርሃነ-ልደቱ አደረሳችሁ!" እያሉን፡ በመስቀልኛና በነዶ መልክ፡ ራሳቸው፡ በሰንበሌጥ ያበጁትን፡ የአበባ ጕንጕን ያበረክታሉ።

፭ኛ፡ በተለይ ቈነጃጅቱ [ልጃገረዶቹ]፡ በኅብረት ኾነው፡ "አበባዪ ሆይ!፥ ለምለም!" የሚለውን የዕንቍጣጣሽ ዘፈን፡ የአውራጇን ድምፅ ተከትለው እየተቀባበሉ፡ "ባልንጀሮቼ! ቁሙ በተራ! እንጨት ሰብሬ፡ ቤት እስክሠራ! እንኳን ቤትና፡ የለኝም ዐጥር! እንዲያው ዐድራለሁ፡ ኮከብ ስቆጥር! ... ባልንጀሮቼ! አትበተኑ! እስክንለማ፡ ዕብራችሁ ኹኑ! ...ባልንጀሮቼ! የለም አትበሉ! የተገኘውን፡ ዐብራችሁ ብሉ!...ባልንጀሮቼ! ዐብረን ዐብረን! ችግር ቢመጣ ተረዳድተን!" እያሉ፡ በየሠፈራቸው ውስጥ፡ በየቤቱ እየተዘዋወሩ፡ መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ። ባለቤቶቹም፡ ያላቸውን የገንዘብ ስጦታ በማበርከት መርቀው ያሰናብቷቸዋል።

፮ኛ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ሰዉ ኹሉ፡ ሴቱም፥ ወንዱም፡ የውስጥ መንፈሱ፡ በደስታ የበዓል ስሜት ተመልቶ፥ የላይ አካሉም፡ በነጭ የክት ልብሱ ተሸልሞ፡ ከሌሊቱ ጀምሮ፡ ወደየሰበካ ቤተ-ክርስቲያኑ ይኼዳል፤ እዚያም፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር፡ ለአዲሱ የምሕረት ዓመት ስላበቃው፡ ምስጋናውን ካቀረበና የምሕረቱ ኪዳን ማረጋገጫ የኾነውን፡ ቅዱስ ቍርባን ከተቀበለ በኋላ፡ ወደየቤቱ ይመለሳል።

፯ኛ፡ በለምለም ሣርና በቄጤማ ጕዝጓዝ፥ በጽጌረዳና በዐደይ-አበባ ተጊጦና በመዓዛው ታውዶ፥ በመልከ-ጼዴቅ ኅብስተ-አኰቴትና ጽዋዓ-በረከት ምሳሌ፡ "ጠበል ጠዲቅ" ተብሎ የተሰየመው [የሚጠራው] እና የተሠየመው [የተሾመው] ዳቦ እና ጠላው፡ ተዘጋጅቶ በሚጠብቀው ቤቱ እንደተገኘና ቤተሰቡ እንደተሰባሰበ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፤ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው ምክንያት፡ እንደኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች፥ ነጋሢዎችና ካህናት በመኾናቸው፡ በእርሱ ጸጋና በረከት፡ "በስመ-እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ!" በሚለው መክፈቻ፡ አራቱን፡ የሃይማኖትና የቃል-ኪዳን፥ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎቶቻችንን አሰምተው በመድገም፡ ከመካከላቸው አንዱ፡ ገበታውን፡ በመስቀል ምልክት፡ በእጁ እያማተበ ይባርካል።

በመጨረሻ፡ ዳቦው ተቆርሶ፡ ተሸንሽኖና በዝርግ ማቅረቢያ ተደርድሮ፡ አዳዩ፡ "በረከተ አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ!" እያለ፡ በዚያ ላለው፡ ለእያንዳንዱ ታዳሚ፡ በትሕትናና በአክብሮት ተመሥጦ እያዞረ ያድለዋል። ተቀባዩም፡ "አሜን!" እያለ፡ በተመሳሳዩ መልክና ይዘት፡ ድርሻውን እያነሣ በመሳም፡ በጠዲቅነቱ፡ በእጁ እየከፈለ ይመገበዋል፤ ጠላውም፡ እንደዚሁ፡ በዋንጫ እየተቀዳ ይታደልና፡ ኹሉም፡ በጠበልነቱ እየቀመሱ ይጠጡታል። ከዚህ በኋላ ነው፡ የበዓሉ መሰናዶ የኾነው ግብዣ የሚቀልጠው።

፰ኛ፡ እስከመስቀል በዓል ድረስ ባሉት ኹለት ሳምንታት ውስጥ፡ ዘመድ፡ ከዘመዱ፥ ጎረቤት፡ ከጎረቤቱ፥ ወድጅ፡ ከወዳጁ፥ ትልቁም፥ ትንሹም፥ ሴቱም፥ ወንዱም፡ ኹሉም ሲገናኝ፥ እየተፈላለገም፡- "እንኳን አደረሰህ! አደረሰሽ! አደረሰን! አደረሳችሁ!" እየተባባለ፡ ከላይ፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን፡ የምሥራች ሰላምታዎችንና የደስታ መግለጫዎችን ቃላት ሲለዋወጥ፥ በየቤቱም፡ የበዓል ድግሡን እያዘጋጀ፡ ተጠራርቶ ሲገባበዝ፥ እንግዶችንና ደኾችን ሲያበላ ይሰነብታል።

፱ኛ፡ በዚህ ዕለት፡ "ገንና" *("ና" ይጠብቃል)፡* የምንለው፡ የጌታችንና የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕን፡ የልደቱን በዓል ስናከብር፡ ሌሎች ብዙ ትዝታዎች ይመጡብናል። በልጅነት ዕድሜያችን፡ ትዝ ከሚሉን ድርጊቶች መካከል፡ እስኪ አንዳንዶቹን እንጥቀሳቸው!

በእየቤታችን፡ ለበዓሉ ዝግጅት፡ ቀደም ብሎ፡ ጠላው ተጠምቆ፥ በበዓሉ ዋዜማም፡ የገና ዳቦውና እንጀራው ተጋግሮ፥ ወጡም ተሠርቶ፥ ምንጣፉ ተንጥፎና በዚያ ላይ ቄጠማው ተጐዝጉዞ፥ በዓሉ፡ የእግዚአብሔር-እም ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ልደታት የሚዘከሩበትና የሚከበሩበት በመኾኑም፡ በረቡዕና ዓርብ ዕለታት ላይ ቢውል እንኳ፡ ያ ዕለት፤ ፍስክ ኾኖ፡ ዶሮውና ሙክቱ ታርዶ፥ በየጎረቤቱም የተጣለው፡ የፍሪዳው ቅርጫ ሥጋ መጥቶ የሚካኼደው መሰናዶና የሚታየው ሽርጉድ፡ አንዱ ነው።

አዎን! በዚህ ዕለት፡ ሴቱም፥ ወንዱም፤ ትልቁም፥ ትንሹም፡ በቤት ውስጥ ኾነ፡ በውጭ፡ በመንገድ ሲገናኝ፡ ሰላምታው ኹሉ፡ እርስ በእርሱ፡ "እንኳን አደረሰህ! አደረሰሽ! አደረሰን! አደረሰዎ! አደረሳችሁ! አሸጋገረን!" እየተባባለ የሚሳሳመውና ሰላምታ የሚሰጣጣው፥ በሜዳም፡ ጎልማሶች፡ ቡድን ለይተው፡ "በገና ጨዋታ! አይቆጡም ጌታ!" እያሉ፡ መምቻው፡ እንደከዘራ እጄታ ቆልማማ በኾነ፡ በገና ዱላ እና "ጥንድ" በተባለች፡ ድቡልቡል የከብት አጥንት፥ ወይም፡ ከእንጨት፥ ወይም ከጨርቅ በተሠራች፡ ጠጣር ኳስ፡ በሰፊ ሜዳ ላይ የሚያካኺዱት ጨዋታ፡ ትዝ ይላል።

፲ኛ፡ ሌላው ደግሞ፡ በየአድባራቱና በየገዳማቱ፥ በየሰበካውም ቤተ-ክርስቲያን፡ ከዋዜማው ማታ አንሥቶ፡ ካህናቱና ሕዝቡ፡- በግእዙ፡ "**ዮም፡ ፍሥሐ ኮነ! በእንተ ልደተ-ትስብእቱ፡ ለኢየሱስ መሲሕ! እምቅድስት ድንግል ማርያም! ...በጎል ሰከበ! በአጽርቅት ተጠብለለ! እግዚእ፥ ወመድኀን፥ ወሰላም፤ ቤዛ ኵሉ ዓለም፡ ዮም ተወልደ!**" ትርጉሙም፡- "ኢየሱስ መሲሕ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለደባት፡ ይህች፡ የዛሬዪቱ ዕለት፡ ታላቅ የደስታ ቀን ናት! ...እግዚአብሔር፡ ራሱን፡ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ፡ ለፍጥረቱ ኹሉ፡ ድኅነትን [መዳንን] እና ሰላምን ለመስጠት፡ ዛሬ፡ በሰውነት ተወለደ! በበረት ውስጥ ተኛ! በጨርቅም ተጠቀለለ!" የሚል የኾነውን የመልእክት ቃል እያሰሙ፡ ሌሊቱን ሙሉ፡ በዜማና በሽብሸባ በታጀበ ማሕሌት፡ ለቸሩ ፈጣሪያቸው፡ ሲያቀርቡት የሚያድሩት የምስጋና መባዕ ነው። ከዚያም፡ እኩለ-ሌሊት ሲኾን፡ ግብዓተ ቅዳሴ ኾኖ፡ ሥርዓተ ቅዳሴው፡ በካህናቱና በምእመናኑ፡ የቅዱስ ቍርባን መቀበልና ማቀበል ከተፈጸመ በኋላ፡ ያስቀደሰው ሰው ኹሉ፡ ቅዳሴ ጠበል እየጠጣና እየተባረከ፡ ወደየቤቱ በሚመለስበት ጊዜ፡ ያለው መንፈሳዊ ደስታ፡ ትዝታው፡ ከቶ አይረሳም።

እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚህ በዓላችን ጊዜ፡ "**ዮም፡ ፍሥሐ ኮነ! በእንተ ልደተ-ትስብእቱ፡ ለኢየሱስ መሲሕ! እምቅድስት ድንግል ማርያም!**" ማለትም፡ "ይህች፡ የዛሬዪቱ ዕለት፡ ታላቅ የደስታ ቀን ናት! ኢየሱስ መሲሕ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተወልዶባታልና።" የሚለውን የምሥራች ቃል እንለዋወጣለን። ይህ፡ የፍጹም ደስታ መንፈስ፥ የመገለጫውም ሥርዓት፡ የግዝረቱ በዓል እስከሚከበርበት፡ እስከመስከረም ፳ እና የበአተ-መቅደሱ በዓል እስከሚውልበት፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ድረስ፡ በዘመነ-ትንሣኤው መልክና ይዘት ይቀጥላል።

በቤተ-ክርስቲያንና በቤት፥ በአደባባይና በሜዳ የሚካኼደው፡ ይህ፡ የአለባበስና የሰላምታ፥ የጸሎትና የቍርባን፥ የጠበል-ጠዲቅና የመስተንግዶ፥ የጨዋታና የዘፈን ሥርዓት፡ በእያንዳንዱ፡ የዓመቱ በዓል ጊዜ የሚደረግ፡ ቋሚ ወግ ስለኾነ፡ **እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ልጆች የኾንነው፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ ኹላችን፡** ይኸው ባህላችን እንዳይዘነጋ፡ በያለንበት፡ ጠብቀን፡ ልንፈጽመው፥ ለልጆቻችንም እያሳወቅን ልናስተላልፈው ይገባናል።

\+ \+ \+